የሰ/መ/ቁ/55229

ጥር 09 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ መሐዳ ዑመር

**ተጠሪ** ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበውን ጉዳይ በተመለከተ በመጀመሪያ ያየው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዕዳውን ሳይከፍል ከቀረ የገበሬ ማህበር ተረክቦ ለእኔ ያስተላለፈልኝ ማሽን ጉድለት የሌለበት መሆን ሲገባው ከጉድለቱ ጋር ስላስተላለፈልኝ ተከሣሹ ባንክ ከእኛ የወሰደውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ መመለስ ይገባዋል በሚል ባቀረቡት ክስና ክርክር መሠረት ተከሣሹ ገንዘቡን ለከሣሽ መመለስ ይገባዋል በማለት የወሰነ ሲሆን በባንኩ /በአሁኑ ተጠሪ/ የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ቀርቦለት የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ ባንኩ የክስ መቃወሚያ አድርጐ ያቀረበውን የይርጋ ክርክር የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሳያየው አልፎ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ መክፈል አለበት ብሎ የወሰነው ያለአግባብ ነው፡፡ ከተነሣው የይርጋ ክርክር አንፃር ሲታይ ክሱ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

የአሁኗ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርቡ የቻሉ ቢሆንም ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልፀው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በተጠሪው በኩል በጽሑፍ በቀረበው መልስ ላይ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተውበት ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በይግባኙ ያላነሳውን የይርጋ ክርክር እራሱ በማንሳት ውሣኔ ሰጥቷል በሚል የገለፁትን በተመለከተ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ የይርጋው ክርክር መቅረቡን ውሣኔው ስለሚያስረዳ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአሁኑ ተጠሪ በኩል የይርጋ ክርክር መቅረቡ ስለተረጋገጠ የአሁኗ አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የተባለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ሲመረመር፡-

የአሁኗ አመልካች ተጠሪው ለእኔና ለባለቤቴ መጭመቂያ ማሽን አስተላለፈልን የሚሉት ነሐሴ 14 ቀን 1985 ዓ.ም. በተደረገ ውል ሲሆን ተጠሪው ከሌላ ገበሬ ማህበር በዕዳ ምክንያት የተረከበውን ማሽን ስለዋጋው አከፋፈል በውሉ ላይ በማመቻቸት ከፍለን የራሳችን በማድረግ እንድናስቀረው አስተላለፈልን በማለት የሚገልጹት ሽያጭ እንጅ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ አመልካች በውል ተላልፎልኛል የሚሉትን ማሽን እንደተረከቡ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2291 መሠረት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲመረመር በማድረግ ጉድለት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በዚሁ ሕግ ቁጥር 2292 መሠረት ለተጠሪው ማስታወቅ ነበረባቸው፡፡ ካስታወቁ በኋላም በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2298/1/ ላይ በተገፀው መሠረት ክስ ማቅረብ ይችሉ የነበረው ካስታወቁበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረቡ ዕቃው ጉድለት ያለበት ነው ብለው የመክሰስ መብታቸውን ያጣሉ፡፡ አመልካች በማሽኑ ላይ ጉድለት ስለመኖሩ በሕጉ መሠረት በአጭር ጊዜ ለተጠሪው አስታውቀው በተወሰነው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ ቀርቶ የፈፀሙት አንድም ነገር ሣይኖር ከአሥራ ሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ተጠሪው ያስረከበን ማሽን ጉድለት ስላለበት የከፈልነውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ይመልስልን የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ አሥር ዓመት ወደሚለው የይርጋ ክርክር መሄድ ሳያስፈልግ አመልካች ማሽኑን እንደተረከቡ በአጭር ጊዜ እንዲመረመር አድርገው ጉድለት ያለው ስለመሆኑ ለተጠሪው በማሳወቅ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሽኑ ጉድለት ያለበት ነው የሚለውን ክስ ያላቀረቡ ስለሆነ የመክሰስ መብታቸውን አጥተዋል፡፡

የይርጋው ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል በሚል ያነሱትን ክርክር በሚመለከት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በሚያይበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ክርክር ያላቀረቡ ሲሆን የይርጋው ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል የሚለውን ክርክር ያነሱት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ ነው፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329 መሠረት ሊታይ የሚችል አይደለም ብሎ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ ፈጽሟል የሚባለው የሕግ ስህተት የለም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ተጠሪው አስተላልፎልን የነበረው ማሽን ጉድለት ስላለበት የከፈልነውን ገንዘብ ብር 40,000 ይመልስልን በሚል ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ